# በሙሰኞች ላይ የተወሰደው እርምጃ ኪራይ ሰብሳቢነትን የመዋጋት ስትራቴጂ አካል ነው

ክፍል ሁለት

ኢብሳ ነመራ

ወደ ፕ/ር በየነ አስተያየት ስመለስ "ኢህአዴግ ለአባላቱና ለደጋፊዎቹ አገር እንዲበዘብዙ ድጋፍ ሰጥቷል" ብለዋል፡፡ ከላይ ከተገለጸው የኢህአዴግ ኪራይ ሰብሳቢነትንና ሙስናን የመከላከል ቁርጠኝነት አኳያ ሲታይ ይህ የፕ/ር በየነ አስተያየት ፍጹም መሰረተ ቢስና ኃላፊነት የጎደለው ነው፡፡

ኢህአዴግ ለደጋፊዎቹና ለአባላቱ ሕግ ከሚፈቅደው ውጭ የሰጠው አንድም የተለየ መብት የለም፡፡ ይሁን እንጂ አባላቱና ደጋፊዎቹ የሆኑ ሰዎች ሙስና ውስጥ የተዘፈቁበት ሁኔታ አለ፡፡
ቀደም ሲል እንደገለጽኩት አባላቱም ሆኖ ደጋፊዎቹ ሙስና ውስጥ ተዘፍቀው ሲገኙ ምንም ማያወላዳ እርምጃ ሲወስድ ቆየቷል፡፡ ከአቶ ታምራት ላይኔ፣ ከአቶ ስዬ አብርሃ በላይ ኢህአዴግ አለ እንዴ?

የፕ/ር በየነ ጴጥሮስ ፓርቲ መድረክ ግን ገገሯ ፓርቲ "ሙሰኞች ናቸው" ብሎ ማይሸሽግ አግልፍ የሰጣቸውንና ያስቀጣቸውን አቶ ሥዬ ፍርድ ቤት የቀረበባቸውን ጥፋተኛ አስብሎ ያስቀጣ ማስረጃ እያወቁ፣ "የታሠሩት በፖለቲካ ምክንያት ነው" ብለው ሽፋን ሠጥተው አቅፈዋቸዋል፡፡

እርግጥ ሙስና ሥልጣን ላይ ባሉ ሰዎች ሥልጣንን ሽፋን በማድረግ በሚሥጢር የሚሠራ በመሆኑ ከኢህአዴግ አባላትና ከደጋፊዎች መሃከል እስካሁን ሳይነቃባቸው ተሸሽገው ያሉ ሙሰኞች ሊኖሩ ይችላሉ፡፡ እነዚህን የተደበቁ ሙሰኞች አጋልጦ ሕግ ፊት ለማቅረብ ሕዝብ፣ ፕ/ር በየነም እንደግለሰብ፣ ፓርቲያቸውም በማስረጃ አስደግፈው ጥቆማ የሚያደርጉበት ስረአት ተዘርግቷል፡፡

ይህም ሆኖ ገገሯ ፓርቲ በበርካታ አጋጣሚዎች በተለይ አባላቱ በመስና ውስጥ መዘፈቃቸውን የሚያመለክት መረጃ ኖሮት በፍርድ ቤት ክስ ለመመስረት የሚያበቃ ማስረጃ በሚያጣበት ሁኔታ

በግምገማ ከፓርቲው ሲያግድ፣ ከመንግሥት ኃላፊነታቸው ሲያነሣ ነዉ የቆየው፡፡ መረጃ ኖሮት ማስረጃ በሚያጣበት ግዜ እንኳን አስተዳደራዊ እርምጃ ይወስዳል፡፡

ፕ /ር በየነ የሠሞኑን እርምጃ "ዋናውን የሙስና ሠንሰለት ለመበጣጠስ የተጀመረ እንቅስቃሴ ነው ለማለት ገና ነው" ብለዋል፡፡

ከዚህ ቀደም ከነበረው ሁኔታ አኳያ ስንመለከተው ለመንግስትና ለገዢው ፓርቲ ኢህአዴግ ሙስናን የመከላከልና የመዋጋት ስራ በአንድ ወቅት በሆይሆይታ የሚወርድበት፣ ከዚያ ጨረስኩ ብሎ የሚተወው ቦግ እልም የሚል ሠሞነኛ የዘመቻ ሥራ አይደለም፡፡ ሙስናን መቆጣጠር ሁሌም የሚሠራ የማያቋርጥ ሥራ ነው፡፡ የተከሰተን ሙስና ከመቆጣጠር ባሻገር ከባለፉት ሥርዓቶች የተወረሰውን ሙስናን የሚሸከም ባሕል ለማስወገገድ በስነምግባር የታነናፀ ሙስናን የሚፀየፍ ትውልዱ ለመፍጠር ትኩረት ሰጥቶ እየሰራ ነው፡፡

ስለዚህ ፕ/ር በየነ "ዋናውን የሙስና ሠንሰለት ለመበጣጠስ የጀመረው ነው ለማለት ገና ነው" ሲሉ የገለፁት ትርጉመ አልባ ነው፡፡ ፕ/ር በየነ "ኢህአዴግ በፖለቲካ በዲፕሎማሲው ሲጨንቀው ነው በባለስልጣናቱ ላይ እርምጃ የሚወስደው፤ በማንም ላይ ቢሆን መረጃ እስካለ ድረስ እርምጃ ለመውሰድ ግዝጁ ነኝ የሚል የፖለቲካ ጫወታ አለው፡፡" ብለውናል፡፡

ልብ በሉ በአንድ ወገን አገሪቱ ውስጥ በተለይ በገዢው ፖርቲ አባላትና ደጋፊዎች ዘንድ ሙስና ተስፋፍቷል የሚሉት ፕ/ር በየነ፣ በሙስና ወንጀል ፈፃሚዎች ላይ የተወሰደውን እርምጃ በሙሉ ፖለቲካዊ ነው ሲሉ ያጣጥሉታል፡፡ ለእርሣቸው መንግስት በሙስና እርምጃ የሚወሰድባቸው ሠዎች በሙሉ ከህወሃት ጋር የተጋጩ ናቸው፡፡ ለዚህ ግን አንድም ማስረጃ አያቀርቡም፡፡ አቶ ታምራት መቼና በምን ጉዳየ ላይ ነበር ከሕወሃት ጋር የተጋጩት? ፕ/ር በየነ ለዚህ መልስ የላቸውም፡፡ ቃለመጠይቅ ያደረገላቸው ጋዜጠኛም እንደመጣላቸው የተናገሩትን ተቀብሎ ከማራገብ ያለፈ እንዴት ብሎ የመጠየቅ አቅምና ፍላጐት ያለው አይመስልም፡፡

በጣም የሚያስገርመው ፕ/ር በየነ ሰሞኑን በአቶ መላኩ ፈንታ፣ በባልደረቦቻቸውና አባሪዎቻቸው ላይ የተወሰደውን በሙስና ወንጀል ተጠርጥረው በቁጥጥር ሥር መዋል ሙስናን ለማዋጋት እንደተወሰደ እርምጃ እንደማይቀበሉት ከወዲሁ እየተናገሩ ነው፡፡

ይህን አስመልክተው "ሠሞኑን ኢህአዴጐች ጉባኤ እያካሄዱ ነበር፤ ይህ እርምጃ ደግም ከጉባኤው ተከትሎ የመጣ ነው፡፡ ከዚህ አንፃር የፖለቲካ ጉዳይ እንዳለበት ምልክት ሊሆን ይችላል" ነበር

ያሉት፡፡ ልብ በሉ "ተጠርጣሪዎቹ በቁጥጥር ሥር የዋሉት በሙስና ወንጀል አይደለም" የሚል ውዠንብር እየፈጠሩ ነው፡፡

የተጠርጣሪዎቹን በቁጥጥር ሥር መዋልን ተከትሎ የሥነምግባርና ፀረ ሙስና ኮሚሽን በሰጠው መግለጫ፣ ተጠርጣሪዎቹ ላይ ከሕዝብ የተሰጠን ጥቆማ መነሻ በማድረግ በከፍተኛ ሚስጥር የተጠርጣሪዎቹን ሕገመንግስታዊ መብት ሣይነካ ክትትል ማካሄድ የተጀመረው ከሁለት ዓመት በፊት ነው፡፡ ከቀድሞው ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ ሕልፈት በፊት  የምስጢራዊው ክትትል ሪፖርት ቀርቦላቸው ነበር፡፡

ፐ/ር በየነ ከአንድ ወር በፊት ከተካሄደው የኢህአዴግ 9ኛ ድርጅታዊ ጉባኤ ማግስት የተወሰደ እርምጃ አስመስለው ያቀረቡት ይህን ከሁለት አመት በፊት የተጀመረ ስራ ነው፡፡ እስከሚታወቀው ድረስ በኢህአዴግ ድርጀታዊ ጉባኤ ላይ ከአቶ መላኩ ፈንታ ጋር አንድም የአቋም ልዩነት አልተነሣም፡፡

የፐ/ር በየነ አስተያየት ገዢውን ፓርቲ አሣጣለሁ ብለው ፣ ሙስናን ለመከላከል የተወሰደውን እርምጃ እንበነ እርምጃ መውሰድ ያቃታቸው ከምክናያታዊንት ይልቅ ብጭፍን ጥላቻ ላይ የተመሰረተ አቋም ስላላቸው ነው፡፡ ይህ ደግሞ ለአገር የሚያስብ የቅን ፖለቲከኛ ባህሪ አይደለም፡፡ ሙስና ተስፋፍቷል በሚለውም ሙስናን ለመዋጋት የተወሰደውንመ እርምጃ በመቃወም በሁለት ተጻራሪ አካሄድ ተመሳሳይ የፖለቲካ ትርፍ ለማግኘት ነው የሞከሩት፡፡

ፐ/ር በየነ ሰዎቹ  የታሰሩት በሙስና ወንጀል ተጠርጥረው ሳይሆን በፖለቲካ አቋማቸው ነው በማለት አፋቸውን ሞልተው መናገራቸው አላሸማቀቃቸውም፡፡ "እርምጃው በዚህ ላይ የሚያቆም ከሆነ በመሰረቱ የሚያደላው ፖለቲካዊ ፋይዳው ነው፡፡" ብለዋል፡፡ ይህን ሲሉ ምን ለማለት እንደፈለጉ በግልጽ አይታወቅም፡፡

"እርምጃው በዚህ ከቆመ ውሳኔው ፖለቲካዊ ነው" ለማለት ፈልገው ከሆነ፣ በሙስና ወንጀል የተጠረጠረሩ ግለሰቦችን በቁጥጥር ስር አውሎ ፍርድ ቤት የማቅረብ ጉዳይ አሁን የተጀመረ ባለመሆኑ እንደ አዲስ ከመታየት ይልቅ፣ ቀደም ሲል  የተጀመረ ሙስናን የመከላከል ቀጣይ እርምጃ ተደርጎ መወሰድ ያለበት መሆኑ መታወስ ይኖርበታል፡፡ እርምጃው የሚቀጥለው "በሙስና ላይ እርምጃ እየተወሰደ ነው" የሚል ምስል ለመስጠት ሳይሆን፣ እርግጥ ሙስናን ለመከላከል በመሆኑ በማስረጃ ላይ የተመሰረተ ክትትልና በማስረጃ ላይ የተመሰረተ ክስ ለወደፊትም ይቀጥላል፡፡

ፐ/ር በየነ አስተያየታቸውን ቀጥለው "በእኛ እምነት ይሄ ሁሉ ከበርቴ ሚሊየነርና ቢሊየነር ዝም ብሎ እየፈላ ያለው የሃገሪቱን ሕዝብ ሃብትና ገንዘብ እየበዘበዘ ነው፡፡ አብዛኛውን እዚህ ያደረሰው ሙሰኝነት ነው፡፡" ብለዋል፡፡

ፐ/ር በየነ ኢትዮጵያ ውስጥ ያለውን ባለሃብት አንዱን ከሌላው ሳይለዩ ሁሉንም የአገር ውስጥ ባለሃብት "የህዝብ ሃብት የዘረፈ ነው" የሚለው ፍረጃቸው ለባለሃብቶች ያላቸውን ዝቅተኛ ግምት ያሳያል፡፡ አሳፋሪ ፍረጃም ነው፡፡ ይህ አመለካካት ምናልባት በወጣትነት ዘመናቸው ያለፉበት "ከሁሉም ሃብት ጀርባ ብዝበዛ አለ" ከሚል የኮምኒስት አመለካካት የመነጨ ሊሆን ይችላል፡፡ አሁን የአገሪቱ የኢኮኖሚ ስርአት የተመሰረተበትን መርህ በዚህ ኮምኒስታዊ መርህ መተንተን ስለማይቻል ይህም እምነታቸው ቢሆን ከስህተት ነጻ አያደርጋቸውም፡፡

እርግጥ በሙሥና ሃብት ያፈሩ ሚሊየነርናና ቢሊየነር ለመሆን የበቁ ባሃብቶች  አሉ፡፡ እሰከአሁን ተሸሽገወ ያሉትን ያህል የሕዝብና የመንግስት መሬት በመቸርቸር፣ በአራጣ አበዳሪነት … ሚሊየነርና ቢሊየነር መሆን የቻሉ ባለሃብቶች ባለፉት አመታት ክስ ተመስርቶባቸዋል፡፡  ከእነዚ|ህ መሃከል የተቀጡም አሉ፡፡

ኢህአዴግ የዚህ አይነት በዝባዥ ባለሀብቶች መኖራቸውን ያምናል፡፡  ባለሀብቶቹን ልማታዊና ኪራይ ሰብሳቢ ብሎ በሁለት የሚከፍለውም ለዚህ ነው፡፡ ኪራይ ሰብሳቢነት ላይ እርምጃ ለመውሰድ ቆርጦ የተነሣውም ለዚህ ነው፡፡

ፐ/ር በየነ የሰጡት አስተያየት ላይ ይህን ያህል ካልኩ አሁ ደግሞ ዶ/ር መራራ ጉዲና የሰሞኑን የሙስና ተጠርጣሪዎችን መነሻ በማድረግ ወደሰጡት አሰተያየት ልመለስ  ፡፡ ዶ/ር መራራ ለኢትዮ ቻናል ጋዜጣ የግንቦት በ10፣ 2005 ዓ/ም እትም ላይ ከሰጡት አስተያየት በተለይ አንድ ጉዳይ ላይ አተኩራለሁ፡፡ ይህም " እርምጃው ተባራሪ ይሁን አቅጣጫ ያለው የጸረ ሙስና ዘመቻ ገና ገና አልለየም" በሚል የሰጡት አስተያየት ነው፡፡

ዶ/ር መረራ ግልጽ ያልሆነላቸው ወይም ሆን ብለው ሊክዱት የሚፈለጉት "መንግስት ኪራይ ሰብሳቢነት (ሙስና) የስርአቱ አደጋ ነው" የሚል አቋም ይዞ የኪራይ ሰብሳቢነት ፖለቲካል ኢኮኖሚን መታገል የጀመረ መሆኑን ነው፡፡ ይህ በስትራቴጂ ደረጃ ያለ የኪራይ ሰብሳቢነት ወይም የሙስና ትግል ነው፡፡

ይህን ስትራቴጂ ተግባራዊ ለማድረግ ባለፈው አመት ሙስና የተስፋፋባቸው ዘርፎች ተለይተዋል፡፡ ከእነዚህ መሃከል የመሬት አስተዳደር እና የገቢዎችና ጉመሩክ መስሪያ ቤቶች ተጠቃሾቸ ናቸው፡፡ ከመሬት አስተዳደር ጋር በተለይ በከተማ መሬት አስተዳደር ዙሪያ የተስፋፋውን ኪራይ ሰብሳቢነትና ሙስና ለመዋጋት ከአንድ አመት በፊት አዲስ የመሬት አስተዳደርና የባለይዞታነት አዋጅ እንዲወጣ ተደርጓል፡፡

ከዚሁ ጋረ ተያይዞ በተለይ ከመሬት ጋር የተያያዘ ሙስና በተስፋፋባቸው ኢዲስ አበባ ከተማና በኦሮሚያ ክልል ፊንፊኔ ዙሪያ ልዩ ዞን በርካታ የከተማ ከንቲቦች፣ መሃንዲሶች፣ ደላሎችና ሌሎች ተባባሪዎች በቁጥጥር ስር ውለው ሕጋዊ እርምጃ ተወስዶባቸዋል፡፡

ይህ ሁኔታ የሰሞኑ ሙስናን የመከላከል እርምጃ ድንገት በዘፈቀደ የተወረወረ ሳይሆን የኪራይ ሰብሳቢነት ፖለቲካል ኢኮኖሚን የመዋጋትና ልማትን የማስፈን ስትራቴጂ ላይ ተመስርቶ በበቂ ዝግጅትና ክትትል የተወሰደ እርምጃ ነው፡፡